ዶ/ር ሥርግው ካስተማሩኝ ብዙ ጊዜ ቢሆንም ስለሳቸው የማይረሱ ትዝታዎች አሉኝ። የሳቸው ተማሪ የነበርኩበት በ፲፱፻፷፮ ዓ. ም. የመጀመሪያው ሴሚስተር ሲሆን የሚሰጡን ኮርስም የጥንታዊቷና የመካከለኛዋ ዘመን ኢትዮጵያ ታሪክ ነበር። ለኮርሱም መማርያ የሚሆን መጽሐፍ /ቴክስት ቡክ/ በተመሳሳይ ርዕስት አዘጋጅተዋል። ኮርሱን ማስተማር ሲጀምሩ ነበር ለመጀመሪያ ጊዜ ያየሁዋቸው። ስለተክለሰብዕናቸው አያሌ ትዝታዎች ቢኖረኝም አሁን የምጠቅሳቸው እጅግ ጥቂቶቹን ነው።

መጀመሪ ካየሁዋቸው ጊዜ አንስቶ እስከ ኮርሱ መጨረሻ ድረስ ይገርመኝ የነበረው አለባበሳቸው ነበር። ሽክ ያሉ ነበሩ። ሙሉ ሱፍ ከነክራባቱ ነበር ሁል ጊዜ የሚለብሱት። ሱፉም፣ ሸሚዙም፣ ከረባቱም ከፍተኛ ጥራት የነበረው ይመስለኛል። ጫማውም እንዲሁ።

የዶ/ር ሥርግው ጠንቃቃነት በአለባበሳቸው ብቻ አልነበረም። ሰዓት አጠባበቃቸው አስገራሚ ነበር። ልክ ኮርሱ በተመደበለት ሰዓት የትምህርት አዳራሻችን /ሌክቸር ሆል/ ውስጥ ይገባሉ። ምናልባት ሰዓት አይተው ሊሆን ይችላል ከቢሮአቸው የተነሱት ያሰኝ ይሆናል። በግሌ ይገርመኝ የነበረው ግን ሲጨርሱ ልክ በሰዓቱ ነበር። ከሌክቸር መቅረት የሚባል ነገር አያውቁም፤ አንዴም ሳይቀሩ ነበር ትምህርቱን የጨረስነው።

ከሁሉም በላይ በአምሮዬ ውስጥ ያለው ትዝታዬ ግን የዕውቀታቸው ጥልቀት ነበር። በዘመኑ ላይ የተጻፉት የምሁራንም ሆነ የብራና መጻሕፍትን ጠንቅቀው ያውቁ ነበር። ይህንንም ማወቅ የምንችልበት ሲያስተምሩ ብቻ ሳይሆን ጥያቄ ስንጠይቃቸው፤ ጥናታዊ ወረቀቶቻችንን በምንሰራበት ጊዜ ስናማክራቸው ወረቀቶቻችንንም ሲያርሙ በሚጽፉዋቸው ማስታወሻዎች ነበር። ለአገራችን ታሪክ ብቻ ሳይሆን ለትውፊታዊ ቅርሶቻቸው ታላቅ አክብሮት ነበራቸው። እኛም እንዲኖረን በእጅጉ ይጥሩ ነበር፤ ባብዛኛው አልተሳካላቸውም እንጂ። ለምሳሌ አንድ የማስታውሰው የሚያበሳጫቸው ነገር ስለንግስተ ሳባ ጉዳይ የተማሪዎቻቸው አስተሳሰብ ነበር። ባብዛኛው ተማሪዎቹ ተረት ተረት ነው ብለው ያጣጥሉት ነበር። በዚህም በጣም ያዝኑ ነበር። ስለ ቅዱስ ያሬድም እንዲሁ። በሱና ከሱ በኋዋላ በተነሱ የቤተክርስቲያን አባቶች ስለተደረሰው ቅዳሴ፣ ስለተለያዩ የቅዳሴ የዜማ ዓይነቶች፣ ስለጣዕማቸውና በተለይም ስለቅኔዎቹ ውበትና ጥልቀት ሌክቸር ሲያደርጉ የከረረ ተቃውሞ ይነሳባቸው ነበር። እሳቸው ግን አይቆጡም ነብር፤ ረጋ ብለው ለማስረዳት ይሞክሩ ነበር። ጊዜው አብዮት ሊፈነዳ ጥቂት ወራት የቀሩት የነበረ ስለሆነ በተማሪዎች መሀል የግራ ርዕየተ ዓለም የበላይነት የሰፈነበት ወቅት ነበር። የእሳቸው አመለካከት ግን ከሀ እስከ ፐ ኮሙኒዝምን የሚቃወም ስለነበረ በተማሪው ተቀባይነት ባያገኝ አይገርምም። እጅግ ያሳዝናቸው እንደነበር ሳልጠቅስ ግን ማለፍ አልፈልግም። ይህንን የምለው በግምት ሳይሆን ኮርሱን በሚሰጡት ጊዜና ከዛም ከጥቂት አመታት በኋላ አግኝቻቸው በግል አጫውተውኝ ነበርና ነው።

በዛ ጊዜ እንደመማሪያ መጽሐፍ (textbook) እንጠቀም የነበረው ራሳቸው የጻፉት Ancient and Medieval Ethiopian History to 1270 የተሰኘውን መጽሐፍ ነበር። ይህ መጽሐፍ ዛሬም ያገለግላል፤ ወደፊትም እንደሚያገለግል ግልጽ ነው። ይህም የሆነበት መጽሐፉ ሰፊና ጥልቀት ባለው ምርምር ላይ ተመስርቶ በመጻፉ ነበር። ደራሲው በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ውስጥ የሚገኙትንም የብራና መጻሕፍት በሰፊው አገላብጠው ስለነበር መጽሐፉን ለማበልጸግ ረድቶአቸዋል። ሰፊ ምርምር ለማድረግ ያገዛቸው ብዛት ያላቸው የውጭና የአገር ውስጥ ቋንቋዎች ማወቃቸው ነበር።

ትምህርቴንም ከጨረስኩ በኋላ እሳቸው ያዘጋጁትን የቤተክርስቲያን መዝገበ ቃላት በተደጋጋሚ አገላብጬ ስለነበር ዶ/ር ሥርግው ምን ያህል ስለ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን፣ ስድባራቱና ገዳማቱ ሰፊና ጥልቅ እውቀት እንደነበራቸው መመዝገብ ችያለሁ። በርግጥም በዶ/ር ሥርግው ሞት ቤተሰባቸው

ብቻ ሳይሆን፣ ዘመድ ወዳጆቻቸው ብቻ ሳይሆኑ እኛም በኢትዮጵያ ታሪክ መስክ ውስጥ ያለነው የሥራ ባልደረቦቻቸውና የቀድሞ ተማሪዎቻቸው ታላቅ የታሪክ ምሁር፤ ታላቅ መምህር አጥተናል።

ተባባሪ ፕሮፌሰር ሽፈራው በቀለ
አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
የፕሮፌሰር ሥርግው ሐብለ ሥላሴ የሰማንያ ቀን መታሰቢያ
ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል
አዲስ አበባ
መጋቢት ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ. ም.